# <u>ፖለቲካ ምስጢሩ</u>

ሰይፉ መታፈሪያ (1984)

ብዙ ብዙ ፤ብዙ ብዙ ታሰረ
በፖለቲካ
አሥሮ የነበረ
በፖለቲካ
ዘብ ቅይይር
ድርጊት መዘርዘር
መቁጠር፤
ነገር እያናናደ
አልተወደደን እያስወደደ
እሥር ቤት፡፡
እሥር ቤት መውለድ
መቀመጥ
ጭጭ--መፋጠጥ
ከባዶ አየር፤
ብቻ መነጋገር
እና መንጠራራት
በከፍ--ከፍፉ
ወደ ነገር አፋፉ፤
አሁንም መንጠራራት
እንዲያ---’ንዳሉ
ነገን ለማየት
ማግሥትን
የወዲያ በኩልን
እዛሬ ላይ ቆሞ
ስሜት አስታሞ
የራስን፤
ድብቁን መለማመጥ
ምሥጢር ሲገለጥ፤
ጠንቁዋይ እንደ መጠየቅ
የሌላውን ዓመት ዘንድሮ ለማወቅ፡፡

<u>ፍርሀትና ናፍቆት</u>

ፈቃደ አዘዘ (ግንቦት 1982)

" ሊመጣ ነው!"  ሲሉኝ " የመቅሠፍት ጊዜ የመከራ ዘመን!"
" የት ደርሷል?"  ስላቸው፤
" ቀርቧል!" ብቻ እያሉኝ፤
"መች ይመጣል?" ስል
" ደርሷል!" ብቻ እያሉኝ፤

ይኸው አርባ ዓመቴ፤በፍርሃት አለሁኝ፡፡
ወይ ዘመኑ መጥቶ ደቁሶ አልደቆሰኝ፤
ፍርሃቱ ፤ ፍርሃቱ፤ ፍርሃቱ ገደለኝ፡፡

----------------//---------------

" ሊመጣ ነው!" ሲሉኝ " የሰላም የደስታ፤የጥጋብ ዘመን!"
" የት ደርሷል?" ስላቸው፤
" ተቃርቧል!" እያሉኝ
" መች ይመጣል?" ም ስል፤
" ተዳርሷል! " እያሉኝ፤

ይኸው አርባ ዓመቴ ፤ በናፍቆት አለሁኝ፡፡
ወይ ዘመኑ መጥቶ በደስታ አላሻረኝ
ናፍቆቱ፤ ናፍቆቱ፤ ናፍቆቱ ገደለኝ፡፡